የወላጅና ፡ ያሳዳጊ ፡ ወረታ ።

አንድ ፡ መካን ፡ ሰው ፡ ነበረ ። በኖረበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልጅ ፡ ስላልነበረው ፡ በመካንነቱ ፡ ሲያዝንና ፡ ሲተክዝ ፡ ይኖራል ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሄድ ፡ ሰውዬው ፤ በሥጋ ፡ የወለዱኝን ፤ በትምህርት ፡ ያሳደጉኝን ፡ አባት ፡ እናቴን ፡ አቤቱ ፡ የሰማይ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፤ ነፍሳቸውን ፡ ማር ልኝ ። ከአባቶቻቸው ፡ ከነአብርሃም ፡ ከነሙሴ ፡ በነፍስ ፡ ከዕረፍት ፡ ቦታ ፡ ዐሳርፋቸው ። ይቅር ፡ ባይ ፡ ነህና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ። ምሕረትህ ፡ ለዘላለም ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሲያመሰግን ፡ መካኑ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እሬ ፡ ልጅ ፡ የለኝ ፡ በሞትሁ ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ ይለምንልኛል ፡ ማንስ ፡ ስሜን ፡ ይጠረዋል ። ስለ ፡ ኃጢአቴ ፡ ብዛት ፡ ነው ፡ ልጅ ፡ ያልሰጠኝ ፡ ፈጣሪዬን ፡ በደልሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነውና ። ይቅር ፡ ቢለኝ ፡ ይችል ፡ የለምን ፡ እያለ ፡ እያስተነተነ ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደረሰና ፡ ጎዘኑን ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ ቢያመለክት ፡ እግዚአብሔር ፡ የለመኑትን ፡ የማይነሣ ፤ የነገሩትን ፤ የማይረሳ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ልክ ፡ በተናገረው ፡ በዓመቱ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ሕጻን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አስተምሮ ፡ ልጇ ፡ ሆይ ፡ የተባረክህ ፡ ሁን ፤ አምላክህን ፡ ፍራ ፤ ዘወትር ፡ በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ አገልጋይ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ጋራ ፡ አገናኘው ። ልጁም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ሆነ ፡ ይባላል ።

አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የለመኑትን ፡ ይሰጣል ። መማርም፡ መልካም ፡ ነው ። ካልተማሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅና ፡ መፍራት ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያስተማሩ ፡ ያሳደጉት ፡ ወላጆቹን ፡ ያመስግን ። ስለነርሱም ፡ ምሕረትን ፡ ይለምን ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ መገሥሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅና ፡ መፍራት ፤ አገርንና ፡ ንጉሥን ፡ መውደድና ፡ ማክበር ፡ ነው ።

ችን ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፤ ዘወትር ፡ ከእብለት ፡ መራቅ ፤ የሚ
ጠቅመውን ፡ አዲስ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ እንደሚያስፈልግና ፡ እንደ ፡ ተለ
መደ ፡ ሁሉ ፡ መያዝ ፤ ሰውን ፡ አለማማት ፤ በማናቸውም ፡ ነገር ፡
አለማዘን ፤ ማንንም ፡ ጎጢአተኛ ፡ አለማድረግ ፤ በየትኛውም ፡
ነገር ፡ ራስን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለመናገር ፡ ነው ።

የሥጋዊን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መብልን ፡ መጠጥን ፡ ልብስን ፡ መኝ
ታን ፡ አሽከርን ፡ በእውነት ፡ ከሚያስፈልጉህ ፡ በቀር ፡ አታስቀ
ምጥ ። ደግሞ ፡ ቀን ፡ የሠራኸውን ፡ ሥስት ፡ ጊዜ ፡ በአሳብህ ፡ ሳት
መረምር ፡ በዐይኖችህ ፡ እንቅልፍ ፡ አይዙር ። ራስህን ፡ እንደዚህ ፡
ብለህ ፡ ጠይቀው ። ወዴት ፡ ውዬ ፡ ነበር ። ከደስታ ፡ ለመድረስ ፡
ሥራና ፡ ትዕግሥት ፡ ያሻል ። ደግሞ ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ይሆነኛል ፡
ብለህ ፡ የምታኖረው ፡ እንዳለህ ፡ በልክ ፡ መሆንና ፡ መጠንቀቅ ፡
አለብህ ። ከመሰላል ፡ ጫፍ ፡ ለመውጣት ፡ በጣም ፡ በዝግታ ፡ ከደ
ረጃ ፡ ወደ ፡ ደረጃ ፡ መተላለፍ ፡ ያስፈልጋል ። ግን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡
ለመውደቅ ፡ አንድ ፡ መጥፎ ፡ እርምጃ ፡ ይበቃል ።

ብዙ ፡ ነገር ፡ አደርጋለሁ ፡ የሚልን ፡ አትመን ። ስለ ፡ ምን ፡
እሱ ፡ ቀላል ፡ ቀጣፊና ፡ አጥፊ ፡ ነው ። በንግግር ፡ ላይ ፡ ማንንም ፡
እንደ ፡ በላይህ ፡ አስመስለህ ፡ አክብረው ። የምታፍርበትን ፡ አት
ሥራ ። ወደ ፡ ላይ ፡ እይ ፡ እንጂ ፤ ወደ ፡ ታች ፡ አትይ ። በመንገድ ፡
ውሸትን ፡ ስታገኝ ፡ ዙረህ ፡ አትያት ፤ ዕውቀትን ፡ ስታገኝ ፡ ምስ
ጢርዋን ፡ ንጠቃት ። ደግነትን ፡ ስታገኝ ፡ ጠብቃት ። መከራን ፡
ስታገኝ ፡ አስተዛዝናት ።

በንግግርህና ፡ በሥራህ ፡ ጨዋ ፡ ሁን ። ሰውን ፡ አታጥቃ ፤ ዘወ
ትር ፡ ሰውን ፡ ከማሥራት ፡ ራስህ ፡ ሥራ ። ምጽዋት ፡ አድርግ ፤ በም
ክርና ፡ በሥራ ፡ ድሆችን ፡ አግዝ ፤ ወጭ ፡ ገንዘብህ ፡ ከምታገኘው ፡
ይነስ ፤ ሦስት ፡ ፈረሶች ፡ የተራቡና ፡ የከሱ ፡ ከመያዝ ፡ ሁለት ፡ የጠ
ገቡና ፡ የወፈሩ ፡ መያዝ ፡ ይሻላል ።

አንተና ፡ ነገሮችህ ፡ ሁሉ ፡ በውጭና ፡ በግቢ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡
የተስማሙና ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ይሁኑ ። አትጣላ ፤ አትፎካከር ፤
አትኩራ ፤ በሥራህ ፡ በንግግርህ ፡ በአሳቦችህ ፡ በምታደርገው ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ትክክል ፤ እውነተኛና ፡ ሥራን ፡ ወዳድ ፡ ሁን ። ከመ
ጣላት ፡ ካለመተባበር ፡ ከዕብድ ፡ ራቅ ፤ በኩራት ፡ ቢሜኑህ ፡ በት
ዕግሥት ፡ አሳልፈው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ መካን ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፫ኛ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ ካስተማረ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረገ ?

መልካም ፡ አስተዳደግ ።

ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የፈጠረህን ፡ አመስግን ። በንጹሕ ፡ ልብ ፡ ትእዛዙን
ፈጽም ፤ አባትህንና ፡ እናትህን ፡ ዘወትር ፡ አክብር ፤ አገርህን ፡ ውደ
ዳት ፤ ጠብቃትም ፤ ተከላከልላት ፤ ወርቅን ፡ አትጥላ ። ግን ፡ ከወርቅ ፡
በላይ ፡ ደግን ፡ ሥራና ፡ የእውነተኛውን ፡ ክብር ፡ ውደድ ።

እንደዚህ ፡ ሁነህ ፡ ካደግህ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ከወንዝ ፡
ዳር ፡ ያደገ ፡ ቅጠሉ ፡ የማይጠወልግ ፤ ፍሬው ፡ ለሰው ፡ የሚያስደ
ንቅ ፡ ዐይነት ፡ ሁነህ ፡ ትኖራለህ ። በሕይወትህ ፡ ሳለህ ፡ እንድትመ
ሰገንና ፡ እንድትወደድ ፡ ሥራ ። በሞትህም ፡ ጊዜ ፡ እንድትጸድቅ ፡
በብልኀት ፡ ወጥነህ ፡ በትዕግሥት ፡ ፈጽመው ።

ታናሹን ፡ ነገር ፡ አትርሳ ፤ ድር ፡ ቢያብር ፡ አንበሳ ፡ ያስር ፡
ከመዋሸት ፡ ዝምታ ፤ በስርቆት ፡ ከመክበር ፡ መደኸየት ፡ ይሻላል ።
ከሞኞች ፡ ጋራ ፡ ባልንጀራ ፡ ከመሆን ፡ ለብቻ ፡ መኖር ፡ ይሻላል ።
ሰው ፡ በተጣላህ ፡ ጊዜ ፡ ለመጣላት ፡ አትቸኩል ። ግን ፡ በግልጽ ፡
ከመጣብህ ፡ እውነተኛነትህን ፡ እስክታገኝ ፡ ማናቸውንም ፡ ያነሰ ፡
ነገር ፡ ሳትዘነጋ ፡ እንድታሸንፍ ፡ ጠንክር ።

ከምታውቀው ፡ ያነሰ ፡ ተናገር ፤ እንደዚህ ፡ ሁነህ ፡ ከኖርህ ፡
ከሷው ፡ ሦስት ፡ ዐሥር ፡ ታገኛለህ ፤ አሳቦችህን ፡ ለከንፈሮችህ ፡
አደራ ፡ አትስጣቸው ። በሥራህ ፡ ውስጥ ፡ ክፉ ፡ አትጨምር ።
ሥራ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቢያንስ ፡ በመልካም ፡ አሳብ ፡ መመራት ፡
ይገባዋል ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ ብኑን ፡ ነው ። በቶሎ ፡ ተረት ፡ ይሆ
ናል ። በፍጥነትም ፡ ይረሳል ። ታላላቆችና ፡ የታወቁት ፡ ሁሉ ፡
ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ ይረሳሉ ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እናስታውሳቸዋለን ።

ለኛ ፡ የሚያስፈልገን ፡ የቀና ፡ አሳብን ፡ መያዝ ፤ እርስ ፡ በርሳ

፩ኛ ፤ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ በመልካምስ ፡ አስተዳደግ ፡ ምን ፡ ፍሬ ፡ ይገኝበታል?
፫ኛ ፤ የጥበብ ፡ መጀመሪያው ፡ ምንድነው ?

ትምህርት ።

ትምህርት ፡ ሁሉን ፡ ይጠቅማል ፤ ማንንም ፡ አይጐዳም ። ለሀብታሞችና ፡ ለድሆች ፡ ለሁላቸው ፡ ይጠቅማል ። ሠራተኛም ፡ ቢማር ፡ ሥራውን ፡ ያስከብራል ። በራሱም ፡ ብርቱና ፡ ነጻነት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቢማር ፡ አይበቃውም ። እንዲህ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፤ ያን ፡ ተምሮት ፡ የነበረውን ፡ ያጠፋል ። እንዲህ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ትልቅ ፡ ቢሆን ፡ በተማሩት ፡ ጓደኞቹ ፡ መሐል ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ይቆጠራል ። በመጨረሻውም ፡ የሚያነብለትና ፡ የሚጽፍለትን ፡ ይፈልጋል ። በገዛ ፡ ሥራውም ፡ የሚመራውና ፡ የሚያቃናው ፡ ምክርም ፡ የሚሰጠው ፡ ግድ ፡ ያሻዋል ። ብዙ ፡ ዘመናትም ፡ በኖረበት ፡ መጠን ፡ የባሰ ፡ ደንቆሮ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ እየሆነ ፡ የሚማርበትን ፡ ጊዜ ፡ መቼ ፡ ያገኝ ፡ ይሆን ።

ብዙዎች ፡ አይመቸንም ፤ ጊዜ ፡ የለንም ፤ አይሆንልንም ፡ እያሉ ፡ ያመካኛሉ ። በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ ይችላል ፤ ብዙዎች ፡ በትምህርታቸው ፡ ሆነ ፤ በጥበባቸው ፡ ወይም ፡ በሥራቸው ፡ የተመሰገኑ ፤ በሥርዐት ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ሳይገቡ ፡ የተማሩ ፡ ናቸው ።

ጊዜ ፡ አባካኝ ፡ ግን ፤ አንዳች ፡ ነገር ፡ ሳያገኝ ፡ ይቀራል ። ማንበብ ፡ ጊዜን ፡ ማጥፋት ፡ አይደለም ። ደኅና ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሠራተኛም ፡ ቢሆን ፡ የራሱን ፡ ክብር ፡ ያተርፋል ። በሚያውቁትም ፡ ዘንድ ፡ ይከበራል ። ድንቍርና ፡ በምትሸሽበት ፡ ልክ ፡ ጥበብ ፡ ትመጣለች ። ብልኅ ፡ መሆንም ፡ የሚበዛውን ፡ ጊዜ ፡ ደስተኛ ፡ ለመሆን ፡ ነው ።

ማንበብ ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ነው ። የገዛ ፡ ራሱን ፡ አእምሮ ፡ ማበርታት ፡ ማለት ፡ ነው ። ሌሎች ፡ የሰሙትን ፡ መስማት ከተማ ፤ ቀዬት ፡ ጋራ ፡ መሣቀይ ፤ የሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ደግ ፡ ሥራን ፡ ማወቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሰውነታችን ፡ እየለቱ ፡ ጤናና ፡ የሚበቃ ፡ ምግብ ፡ እንዲል ፤ እንዲሁም ፡ ለአእምሮዋችን ፡ የመልካም ፡ ንባብ ፡ ምግብ ፡ ያሻዋል ። ማንበብን ፡ የሚያውቅ ፡ ተራራን ፡ እንደሚወጣ ፡ ሰው ፡ ነው ። በወጣበት ፡ ልክ ፡ የሚያየው ፡ ነገር ፡ እየሰፋለት ፡ ይሄዳል ። እማራለሁ ፡ ብሎ ፡ ዘወትር ፡ ማንበብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ ከፍታ ፡ እንደ ፡ መውጣት ፡ ያህል ፡ ነውና ፡ ብዙዎችን ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ማየት ፡ ነው ።

አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ወዳጅን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማየት ፡ ነው ። ብዙ ፡ የሚያነብ ፡ ብዙ ፡ ያውቃል ። ቢሆንም ፡ ግን ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ ማንበብ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ።

ትንንሾች ፡ ልጆች ፡ ክፉውንና ፡ መልካሙን ፡ ሊለዩ ፡ አይችሉም ። እንዲሁም ፡ በአእምሮ ፡ የደኸዩም ፡ እንደ ፡ ሕጻናት ፡ ናቸውና ፡ የማይጠቅማቸውን ፡ በጣም ፡ ሊያስተውሉ ፡ አይቻላቸውም ። ሰው ፡ በበረሃ ፡ የማያውቀውን ፡ ፍሬ ፡ ወድቆ ፡ ቢያገኝ ፡ የሚበላ ፡ መሆኑን ፡ ባያውቅ ፡ እንዳይጎዳ ፡ አስቀድሞ ፡ ይጠይቃል ። እንዲሁም ፡ መጻሕፍቶችን ፡ መምረጥ ፡ ያስፈልጋል ።

ብዙ ፡ መጥፎዎች ፡ መጻሕፍት ፡ አሉ ። ክፉዎችንም ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ ለነፍስ ፡ እንደ ፡ መርዝ ፡ ናቸው ። ክፉዎችንም ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበብ ፡ በሥጋቸውና ፡ በነፍሳቸው ፡ የጠፉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

የከበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉ ። ብዙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ልጅ ፡ ለወላጆቹ ፡ ሕዝብ ፡ ላገሩና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ባለትዳር ፡ ለትዳሩ ፡ ወታደር ፡ ለሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ሰውም ፡ ለገዛ ፡ ራሱና ፡ ለባልንጀራው ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ የሚያስተምሩ ፤ እንዲሁም ፡ የሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ የእንስሳን ፡ ወገን ፡ (ጐኦሎጊ) የአትክልትን ፡ (ቦታኒክ ፡) የብረትን ፡ ወገን ፡ (ሚራሎጊ) ፡ የከዋክብትን ፡ አስትሮኖሚ) ፡ የምድርን ፡ መለኪያ ፡ ጌኦሜትሪ) የጤንነትን ፤ የእንዱስትሪን ፡ የመካኒክን ፡ የታሪክንና ፡ የእግዚአብርን፡ ቃል ፡ ትምህርት ፡ የሚነግሩ ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ የሚመስሉ ፡ ብዙ ፡ ትምህርቶች ፡ አሉ ። ለሰው ፡ የሚጠቅሙ ፤ እያንዳንዱ ፡

በተፈጥሮው ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ዕውቀት ፡ ሊሠለጥንባቸው ፡ የሚ
የሚገባው ፡ ትምህርቶች ፡ አሉ ። ከሕዝባችንም ፡ ወጣቶች ፡ አንዱ ፡
በዚህ ፤ ሁለተኛውም ፡ በዚያ ፤ ሌላውም ፡ በሌላው ፡ ዐይነት ፡ ትም
ህርት ፡ ይሠልጥን ። የኛ ፡ የገዛ ፡ ራሳችን ፡ ሳይሆን ፡ በብድር ፡ ብቻ ፡
ብንኖር ፤ በብድር ፡ ብቻ ፡ ብንሠራ ፡ ከቶ ፡ አንጠቀምም ። እንግ
ዲህ ፡ ኢትዮጵያችንን ፡ በዕውቀት ፡ ከሚጠቅሟት ፡ አንደኛው ፡
ነገር ፡ ልክ ፡ የሌላቸው ፡ ወጣቶች ፡ በስጦታቸው ፡ በጣም ፡ እንዲ
ሠለጥኑ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ትምህርት ፡ በልጅነት ፡ አበባ ፡ በጥቅምት ፡
የተማረ ፡ ክብሩን ፡ መረመረ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ከትምህርት ፡ ምን ፡ ይገኛል ?
፪ኛ ፤ የንባብ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ?
፫ኛ ፤ በንባብ ፡ የሚገኘውን ፡ ፍሬ ፡ ተናገር ።

ዘይሚህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ጥበበ ።

የሰው ፡ ዐይነቱ ፡ ፫ ፡ ነው ፡ ይባላል ። አንዱ ፡ ብልኅ ፤ ሁለ
ተኛው ፤ የብልኅ ፡ ብልኅ ፤ ፫ኛው ፤ ሰነፍ ፡ ነው ። ብልኅ ፡ የሚባ
ለው ፡ መከራ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ የማይደነግጥ ፤ ልቡናው ፡ የማይበ
ተን ፤ ዕውቀት ፡ የማያጥረው ፤ የሚያመጣው ፡ ብልኀት ፡ የማይጠ
ፋው ፡ ነው ።

የብልኅ ፡ ብልኅ ፡ የተባለው ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጠው ፡ ሰውነቱ ፡
የማይሳሳ ፤ በሚሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚደፍር ፤ የሚመጣውን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ በየዐይነቱ ፡ የሚመልስ ፤ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ ያለው ፤
መከራ ፡ ሳያገኘው ፡ ምናልባት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይመጣብኛል ፡ ብሎ ፡
የሚጠረጥረውን ፡ መከራ ፡ ሳይንቅ ፤ ትንሹን ፡ ስለ ፡ ትልቅ ፡ ቆጥሮ
መከራ ፡ ሳያገኘው ፡ በእውነት ፡ ያገኘው ፡ አስመስሎ ፡ የሚያወጣ
ውን ፡ ብልኀት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ተጠንቅቆ ፡ የመጣውን ፡ ነገር ፡

የሚጠባበቅ ፤ ሕመም ፡ ሳያገኘው ፡ ለደቂ ፡ መድኀኒት ፡ አሰናድቶ ፡
የሚኖር ፤ የሚመጣውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሳይደርስበት ፡ የሚመልስ ፡
ሰው ፡ ነው ።

ሰነፍ ፡ የተባለው ፡ ልሂድ ፡ ልቅር ፡ ላድርግ ፡ ልተው ፡ የሚል ፡
በልቡናው ፡ ቆርጦ ፡ አንዱን ፡ ሳይዘው ፡ በማኻል ፡ ቤት ፡ እየዋ
ለለ ፡ ምኞትና ፡ ቸልታ ፡ ሲያበዛ ፤ ሥራውን ፡ በፍጥነት ፡ ሳይፈ
ጽም ፡ ቀርቶ ፡ ሲጓደድ ፡ ጥፋት ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ነው ።

የሥራ ፡ ደጉ ፡ መጨረሻው ፡ ያማረ ፡ ነው ። ከሴትም ፡ ደጊቱ ፡
የባሏን ፡ ፈቃድ ፡ የምትፈጽም ፡ ናት ። ከምስጋናም ፡ ደጉ ፡ በጻድ
ቃን ፡ በበጎ ፡ ሠሪዎች ፡ አንደበት ፡ የተነገረው ፡ ነው ። ከነገሥታ
ትም ፡ በልዕልና ፡ የሚበልጥ ፡ ንጉሥ ፡ የጥጋብ ፡ ሥራ ፡ የማይሠራ ፡
ኩራትና ፡ ትዕቢት ፡ ያልተዋሐደው ፤ ምክርንም ፡ ለመስማት ፤
የማይኰራ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰምቶ ፡ የሚያደርጉትና ፡ የሚተ
ውት ፡ አለ ። ከባሕርይም ፡ ደጉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፍራት ፡ የሚ
ረዳው ፡ ነው ።

የዚህም ፡ ምሳሌ ፡ የ፫ቱ ፡ ዓሦች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ሦስት ፡ ዓሦች
ያሉበት ፡ የጠራ ፡ ትልቅ ፡ ባሕር ፡ ነበር ። ከነዚያም ፡ ከሦስቱ ፡ ዓሣ
ዎች ፡ አንዲቱ ፡ አእምሮ ያላት ብልኅ ፡ ነበረች ።

ሁለተኛዋ ፡ ከሷ ፡ የበለጠች ፡ ዕውቀት ፡ ያላት ፡ ብልኅ ፡ የብ
ልኅ ፡ ብልኅ ፡ ነበረች ። ሦስተኛዋ ፡ ግን ፡ ዕውቀት ፡ የሌላት ፡ ሰነፍ ፡
ነበረች ። ያም ፡ ትልቅ ፡ ባሕር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በገለልታ ፡ ቦታ ፡ ነበረ ።
አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ የማይደርስበት ፡ ካጠገቡም ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡
ያለበት ፡ ነበረ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ዓሣ ፡ አጥማ
ጆች ፡ በፈሳሹ ፡ አጠገብ ፡ ሲያልፉ ፡ ያንን ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ አዩና ፡
ወደዚያ ፡ ባሕር ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ በሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡
ለማደን ፡ ተቃጠሩ ። ዓሣዎቹም ፡ ያዳኞቹን ፡ ነገር ፡ ሰምተው ፡ አሳ
ባቸውን ፡ ዐወቁ ። ዕውቀት ፡ ያደረባት ፡ የብልኅ ፡ ብልኅ ፡ ያልናት ፡
ያዳኞቹን ፡ ንግግር ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፤ ጠርጥራ ፡ ደንግጣ ፤ ፈርታ ፡
ዛሬ ፡ ነገ ፡ ሳትል ፡ ሳታወላውል ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ ተነሥታ ፡
በጣም ፡ ጥልቅ ፡ ወደሆነው ፡ ክፍል ፡ ሸሽታ ፡ ዳነች ። ሁለተኛዋ ፡
ብልኅ ፡ የተባለችውም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ችላ ፡ ብላ ፡ ከቦታዋ ፡ ተቀ
ምጣ ፡ ሳለች ፡ ሁለቱ ፡ አዳኞች ፡ ዳግመኛ ፡ መጡ ። እሷም ፡ እነ
ሱን ፡ አይታ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ነገር ፡ ዐሳባቸውን ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡

ወንዙ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ በሚገባበት ፡ ቦታ ፡ ለመውጣት ፡ አስባ ፡ በፍ
ጥነት ፡ ሄደች ፤ ግን፡ያንን ፡ ቦታ ፡ አዳኞች ፡ ዘግተውት ፡ አገኘችው ።

እሷም ፡ እነሱ ፡ እንደ ፡ ደረሱባትና ፡ የምታመልጥበት ፡ መው
ጫ ፡ እንዳጣች ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፤ አዝና ፡ ተክዛ ፡ በብዙ ፡ አድርጋ ፡
ተጸጽታ ፡ እጅግ ፡ አድርጌ ፡ አጠፋሁ ፡ አለች ። ቸል ፡ የማለት ፡ መ
ጨረሻው ፡ ይህ ፡ ነው ። ነገሩም ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተፋጥኖ ፡ ባየች
ጊዜ ፡ ምን ፡ ብልኀት ፡ ይገኝልኛል ፡ አለች ። ነገር ፡ ግን ፡ የነገሩን ፡
መፈጸሚያ ፡ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የተገኘ ፡ ምክርና ፡ ጥበብ ፤ የፍ
ጥነት ፡ ዕውቀትና ፡ ብልኀት ፡ እጅግ ፡ አይጠቅምም ። ቢሆንም ፡
አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ችግርም ፡ ቢያገኘው ፡ በፍጥነት ፡
የሚገኘውን ፡ ምክርና ፡ ብልኀት ፡ አይጠቅመኝም ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡
ሳይቆርጥ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ብልኀት ፡ መፈለጉን ፡ አይተውምና ።

ስለዚህ ፡ ዓሣይቱ ፡ የሞተች ፡ መስላ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጀርባዋ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሆድዋ ፡ እየተገለበጠች ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ እያሰፈ
ፈች ፡ ትሄድ ፡ ጀመር ። አዳኞቹ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ባዩ
ዋት ፡ ጊዜ ፤ የሞተች ፡ መስሏቸው ፡ አንሥተው ፡ በትልቁ ፡ ባሕ
ርና ፡ በፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ መሐከል ፡ ባለ ፡ ደረቅ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አስ
ቀመጥዋት ፤ እሷም ፡ ወደ ፡ ፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ ዘላ ፡ ገብታ ፡ አመለጠች።

ሦስተኛዋ ፡ ዕውቀት ፡ የሌላት ፡ ደካማ ፡ ሰነፍ ፡ ግን ፡ ልሂድ ፡
ልቅር ፡ ስትል ፡ አንዱን ፡ ሳትይዘው ፡ በመካከል ፡ ቤት ፡ ስታወላ
ውል ፡ ታድና ፡ ተያዘች ።

ኩኑ ፡ የዋሃነ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፤ ወኩኑ ፡ ጠቢባነ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡
ምድር ፡ የተባለው ፡ ለዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ምሳሌ ፤ ያወቀ ፡ ተጠነቀቀ ። የዘነጋ ፡ ተወጋ ። ዓሣ ፡ በወንዙ፡
ይታረዳል ፤ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ በቤቱ ፡ ይፈርዳል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የሰው ፡ ዐይነት ፡ ስንት ፡ ይባላል ?
፪ኛ ፤ የብልኀ ፡ አኳኋን ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፫ኛ ፤ የሰነፍስ ?
፬ኛ ፤ ከሦስቱ ፡ ዓሣዎች ፡ ያላመለጠችው ፡ የትኛዋ ፡ ናት?
፭ኛ ፤ ምሳሌውን ፡ ተናገር ።

ደግ ፡ ሥራ ።

አራት ፡ ነገሮች ፡ አገኘሁ ። እነሱም ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ፡ የሰ
በሰቡ ፡ ናቸው ፤ መጀመሪያዋ ፡ ጥበብ ፡ ፪ኛዋ ፡ አእምሮ ፡ ፫ኛዋ ፡
ንጽሕና ፡ ፬ኛዋ ፡ ፍርድ ፡ ማስተካከል ፡ ናቸው ።

ዕውቀትና ፡ ትዕግሥት ፡ አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ አደላድሎ ፡
አርቆ ፤ ማሰብ ፡ ከጥበብ ፡ ይቆጠራል ። መታገሥ ፡ (መቻል ፡) ዝግ
ታ ፤ ከአእምሮ ፡ ይቆጠራል ። ሰውን ፡ ማክበር ፡ አፋርነት ፡ ቸር
ነት ፡ ሰውነትን ፡ ከውርደት ፡ ቦታ ፡ መጠበቅ ፡ ከንጽሕና ፡ ይቆጠ
ራል ። እውነት ፡ መናገር ፤ ለሰው ፡ በጎ ፡ መዋል ፡ ደግነት ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ መፍራት ፡ ግብረ ፡ መልካምነት ፡ ከፍርድ ፡ ማስተካ
ከል ፡ ይቆጠራል ። መልካም ፡ ሥራ ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ እነዚህ ፡ ናቸው
ለውጣቸው ፡ ክፋት ፡ ነው ።

የሰው ፡ አእምሮ ፡ የሚፈተነው ፡ በ፮ ፡ ነገር ፡ ነው ። ፩ኛው ፤
ዝግታ ፡ ነው ፤ ፪ኛው ፤ ሰው ፡ የራሱን ፡ ልክ ፡ ዐውቆ ፡ ሰውነቱን ፡
መጠበቅ ፡ ነው ። ፫ኛው ፡ ነገሥታት ፡ የሚጠሉትን ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡
ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ሠርቶ ፡ በቅን ፡ ለነሱ ፡ መገዛት ፡ ነው ። ፬ኛ ፡
ሰው ፡ የምስጢሩን ፡ መጠን ፡ ዐውቆ ፡ ለወዳጁ ፡ ሲያካፍል ፡ የሚ
ገባውን ፡ ነገር ፡ ማወቅ ፡ ነው ። ፭ኛው ፤ በነገሥታት ፡ ደጅ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ አንደበቱን ፡ መጠበቅ ፡ በመልካም ፡ ቃል ፡ በፍቅርና ፡ በት
ሕትና ፡ መናገር ፡ ነው ። ፮ኛው ፤ ሰው ፡ የራሱንም ፡ ቢሆን ፡ የሌላ
ውንም ፡ ቢሆን ፡ ምስጢርን ፡ መቻል ፡ ነው ። ፯ኛው ፤ አንደበቱ ፡
በትክክል ፡ ለመናገር ፡ የሚቻለው ፡ መሆን ፤ መጨረሻውም ፡ በት
ክክል ፡ ማሰብ ፡ ባለማወቅ ፡ አለመናገር ፡ ምሥጢሩንም ፤ ለሚታ
መኑ ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፤ ለማንም ፡ አለማካፈል ፡ ነው ።

፰ኛው ፤ ሰው ፡ በተሰበሰበበት ፡ ቦታ ፡ ባልጠየቁት ፡ ነገር ፡
አለመናገር ፤ ይህም ፡ ባሕሪ ፡ ባንድነት ፡ የተዘጋጀለት ፡ ሰው ፤ ለሰ
ውነቱ ፡ የሚጠቅመውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አያጣም ። ለነፍሱም ፡ በሰ
ማይ ፡ ቤቱ ፡ የሚሆነው ፡ ነገር ፡ አይጐድልበትም ።

የትዕግሥት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ምሥጢርን ፡ መቻል ፡ ነው ።
ምሥጢርንም ፡ ለሚታመን ፡ የነገሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእውነት ፡
ከጥፋት ፡ ይጠብቃል ። ምሥጢርንም ፡ የነገሩት ፡ ሰው ፡ ያንን ፡

ምሥጢር ፡ አውጥቶ ፡ መናገር ፡ አይገባውም ። በሁለቱም ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ምሥጢር ፡ አይደበቅም ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በምሥጢር ፡ ነገር ፡ የተናገሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሁለቱ ፡ አንዳቸው ፡ ፫ኛ ፡ ሳይጨምር ፡ አይቀርም ። ከ፫ኛውም ፡ ሰው ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ በውነት ፡ ተበትኖ ፡ አገሩን ፡ ያደርሰዋል ። ባለቤቱም ፡ ሊክድ ፡ አይችልም ። በሰማይ ፡ ላይ ፡ ተቆራርጦ ፡ እን ደሚታይ ፡ ደመና ፡ ነው ። ፭ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ደመና ፡ ተቆራርጧል ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፡ ፭ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ አሰትህ ፡ ነው ፡ ሊለው ፡ አይ ችልም ።

ከነገሥታት ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ጥቅም ፡ የማይገኝበትን ፡ ሊናገሩት ፡ የማይገባውን ፡ ትርፍ ፡ ቃል ፡ ከመናገር ፡ ዝምታ ፡ ይበልጣል ።

ሥጋህን ፡ በኃጢአት ፡ እንዳያስተው ፡ ለአፍህ ፡ ነጻነትን ፡ አትስጠው ። ሐኪሞች ፡ ሊያድኑት ፡ የማይቻላቸው ፡ ለሰው ፡ ልጅ እጅግ ፡ የሚያስቸግረው ፡ መድኀኒት ፡ የሌለው ፡ በሽታው ፡ ምላሱ ፡ ነው ።

ክፉን ፡ ነገር ፡ በመናገር ፡ በራሱ ፡ ጥፋትን ፡ ያመጣል ። ክፉ ፡ ነገር ፡ ከመናገር ፡ ዝምታ ፡ ይሻላል ። ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ግን ፡ ምሬሃለሁ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ከማለት ፡ ዝም ፡ አይበሉ ።

መምህራንም ፡ ተናገር ፤ እንደ ፡ ከርቤ ፡ እስክትመር ፡ ይላሉ ። ከማስተማር ፡ አትቦዝን ፤ ዝም ፡ አትበል ። ዝምታ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ከመናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በጎውን ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ ዝምታ ፡ አይጠቅምምና ፡ ዝምታን ፡ አትውደዱ ፤ ማስ ተማር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ ሕግ ፡ ነውና ። የታዘዘውን ፡ ልን ፈጽም ፡ ይገባናል ። ወደ ፡ ጥፋት ፡ ተማርከው ፡ የሄዱትን ፡ ትመ ልሷቸው ፡ ዘንድ ፡ አስተምሩ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የሰው ፡ አእምሮ ፡ በስንት ፡ ነገር ፡ ይፈተናል ?
፪ኛ ፤ የሰው ፡ አእምሮ ፡ የሚፈተንበትን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።
፫ኛ ፤ ፫ኛውንና ፡ ፮ኛውን ፡ ተናገር ።

ዝኖንና ፡ ድርጭት ።

ከክፉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የተጎራበተና ፡ የተወዳጀ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ሰው ፡ ነው ።

ከውሃ ፡ መስጠም ፡ ቢድን ፡ ከውሃው ፡ ውስጥ ፡ ካለ ፡ ከሚያስ ፈራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አይድንም ።

ሰውነቱንም ፡ ከጥፋት ፡ የማያድን ፡ አእምሮ ፡ ከሌላቸው ፡ ከእንስሳት ፡ ይቆጠራል ። እንስሳት ፡ እንኳን ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ እንዲፈልጉ ፡ ከሚጐዳቸው ፡ እንዲሸሹ ፡ የደመ ፡ ነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ አላቸው ። ወደሚያጠፋቸው ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ቦታ ፡ ራሳቸ ውን ፡ ሲወስዱ ፡ አላየናቸውም ። ወደሚያጠፋቸው ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ቦታ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ በደመ ፡ ነፍሳቸው ፡ ዕውቀት ፡ ተገንዝበው ፡ ላካላቸው ፡ ሰስተው ፡ ራሳቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲሉ ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ ሸሽተው ፡ ርቀው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ይሄዳሉ ።

አእምሮ ፡ አለኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፤ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ቦታ ፡ የሚያ ደርሰውን ፡ ሥራ ፡ ለምን ፡ ይሠራ ፡ ይሆን ? ያንኑ ፡ የድንቁርና ፡ ዕውቀቱን ፡ አክብሮ ፡ እንጂ ፡ ነው ። የራሴ ፡ ዕውቀት ፡ ይበቃኛል ፡ ብሎ ፡ ብቻውን ፡ የሆነና ፡ ለወዳጁም ፡ ምክርን ፡ ሳያካፍል ፡ ቀርቶ ፡ በዕውቀቱ ፡ ላደረ ፡ ሰው ፡ ረዳት ፡ የለውም ። እሱም ፡ ጠፊ ፡ ነው ።

አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፤ በብልኀቱና ፡ በዕውቀቱ ፡ የሚያገ ኘውን ፡ ነገር ፡ በጎይልና ፡ በብዙ ፡ ፈረስ ፡ ፈልገው ፡ ሊያገኙት ፡ አይችሉም ።

የዚህም ፡ ምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። አንዲት ፡ ድርጭት ፡ ዝኖን ፡ ውሃ ፡ ሊጠጣ ፡ በሚመላለስበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፤ ቤቷን ፡ ሠርታ ፡ ዕንቁላል ፡ ጥላ ፡ ነበረች ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዝኖን ፡ እንደ ፡ ጥንት ፡ ልማዱ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ሲሄድ ፡ የድርጭትን ፡ ቤት ፡ ረግጦ ፡ ዕንቁላሏን ፡ ሰብሮ ፡ አሳዘናት ።

እሷም ፡ ያገኛትን ፡ መከራ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ያደረጋት ፡ ዝኖን ፡ መሆኑን ፡ ዐውቃ ፡ በራ ፡ እያለቀሰች ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ዐረ ፈች ፤ ዝኖኑም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ባንተ ፡ ጥግ ፡ ስኖር ፡ ስለምን ፡ ዕንቁላሌን ፡ ሰብረህ ፡ አሳዘንኸኝ ። ይህን ፡ ሥራ ፡ የሠራኸው ፡ ዐቅሜን ፡ አሳንሰህ ፡ ነገሬን ፡ አቃለህ ፡ ስለእኔ ፡ ንቀት ፡ ብለህ ፡

ነውን? ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ያደረሰኝ ፡ ይኸው ፡ አንቺ ፡ ያልሽው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አላት ። እሷም ፡ ትታው ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ፡ ወፎች ፡ ሠራዊት ፡ ሄደችና ፡ ዝኖኑ ፡ የበደላትን ፡ ነገረቻቸው ። እነሱም ፡ ወፎች ፡ ነን ፡ ምን ፡ እናድርገው ፡ ብለሽ ፡ ነገርሽን ፡ ቢሏት ፤ ጭልፊቶችንና ፡ ቁራዎችን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሄዳችሁ ሁለት ፡ ዐይኑን ፡ እያንቆራችሁ ፡ እንድታጠፉልኝ ፡ እፈልጋለሁ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ብልኀት ፡ ፈልጌ ፡ የማደርገውን ፡ እኔ ፡ ዐውቃለሁ ፡ አለቻቸው ። እነሱም ፡ ፈቃድዋን ፡ ለማድረስ ፡ ወደ ፡ ዝኖኑ ሄደው ፡ ዐይኑን ፡ እያነቆሩ ፡ አጠፉት ።

እሱም ፡ ወደ ፡ ምግቡና ፡ ወደ ፡ መጠጡ ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ አቅቶት ፡ ባጠገቡ ፡ ያለውን ፡ ከመሬት ፡ ያገኘውን ፡ እየለቃቀመ ፡ ሲበላ ፡ እሷም ፡ የሱን ፡ እንዲህ ፡ መሆን ፡ ዐይታ ፡ ብዙ ፡ ዕንቁራሪቶች ፡ ወዳሉበት ፡ ወንዝ ፡ ሄዳ ፤ ዝኖን ፡ የበደላትን ፡ ለነሱ ፡ አዋየች ። እነሱም ፡ ለዝኖን ፡ ጎይል ፡ የምናግዝሽ ፡ ምን ፡ ዐቅምና ፡ ብልኀት ፡ አለን ፡ አሏት ። ወደሱ ፡ ቀረብ ፡ ወዳለችው ፡ ጉድጓድ ፡ ቦታ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሄዳችሁ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቃል ፡ እንድትጮሁ ፡ እፈልጋለሁ ። እሱም ፡ ያለጥርጥር ፡ ውሃ ፡ ያለ ፡ ይመስለውና ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ፡ አለቻቸው ።

እነሱም ፡ የሷን ፡ ፈቃድ ፡ ለማድረስ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ ጮሁ ። ዝኖኑም ፡ የዕንቁራሪት ፡ ድምጥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፤ ያለመጠን ፡ ውሃ ፡ ጠምቶት ፡ ነበርና ፡ በእውነት ፡ ውሃ ፡ ያገኘ ፡ መስሎት ፡ ወደ ፡ ጉድጓዱ ፡ ሄዶ ፡ ወድቆ ፡ ተሰባበረ ። ድርጭትም ፡ መጥታ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ክንፏን ፡ እያራገበች ፡ አንተ ፡ በጎይልህ ፡ የምትመካ ፡ ጥጋበኛ ፡ ሰው ፡ ናቂ ፡ ኩራተኛ ፡ ነገሬን ፡ አቃለህ ፡ ሰውነቴን ፡ እንዳሳነስኸው ፡ ከአካሌ ፡ ማነስ ፡ ጋራ ፡ የብልጣቴን ፡ ትልቅነት ፡ ያንተን ፡ ገዛፍነት ፡ የዕውቀትህን ፡ ማነስ ፡ የልቡናህን ፡ ስንፍና ፡ አየኸውን ? አለችው ።

ሰውን ፡ ስለ ፡ ጉስቍልናውና ፡ ስለ ፡ ድኽነቱ ፡ አትናቀው ። ከአዕዋፍ ፡ ሁሉ ፡ ንብ ፡ ታንሳለች ፤ የሥራዋ ፡ ፍሬ ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ ይጠቅማል ። ቀን ፡ በመጠጡ ፤ ያዘኑትን ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። ሌሊት ፡ ጨለማውን ፡ አጥፍቶ ፡ በብርሃኑ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። በባለጸጎች ፡ ዐይን ፡ ፊት ፡ የተናቀ ፡ ጐስቋላ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብ

ሔር ፡ ዘንድ ፡ የተከበረ ፡ ነውና ። በነፍሳችሁ ፡ ጉዳት ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ድኻን ፡ አትናቁ ፤ አታጉላሉት ፤ በተቻላችሁም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ርዱት ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ እንስሶች ፡ የሚጠቅማቸውንና ፡ የሚጐዳቸውን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያውቃሉ ?
፪ኛ ፤ ድርጭቷ ፡ ወደ ፡ አዕዋፍ ፡ ሄዳ ፡ ምን ፡ አለቻቸው ?
፫ኛ ፡ ወፎቹስ ፡ ምን ፡ አደረጉላት ?
፬ኛ ፤ ዕንቁራሪትዋስ ፡ ምን ፡ ርዳታ ፡ አገኘች ?
፭ኛ ፤ በመጨረሻው ፡ ዝኖኑ ፡ ከምን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ተናገር ።

ሲያዩት ፡ ያምር ፡ ሲይዙት ፡ ይደናገር ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ ሁለቱ ፤ ወንዱ ፡ ከውጭ ፡ በግብርና ፤ ሴቲቱ ፡ ከቤት ፡ በማዘጋጀት ፡ ተስማምተው ፤ ትዳራቸውን ፡ አቃንተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባሏ ፡ በትንሽ ፡ ነገር ፡ በሚስቱ ፡ ተቆጥቶ ፡ « እኔ ፡ በውጭ ፡ በእርሻ ፡ ስደክም ፡ ከበሬ ፡ ጋራ ፡ ስወርድ ፡ ስወጣ ፡ ስሄድ ፡ ስመለስ ፡ እውላለሁ ። አንቺ ፡ ከቤት ፡ ከጥላ ፡ ያለድካም ፡ ተቀምጠሽ ፡ እንደዚህ ፡ ልታላግጭ ፤ በምንስ ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ጐደለ ፤ ይህስ ፡ ስለምን ፡ ሳይሠራ ፡ ቀረ ፡ » እያለ ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ይመረር ፡ ጀመር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ « ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ አትመረር ፤ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ላንተ ፤ አንተ ፡ የምትሠራውን ፡ ለእኔ ፡ እንለዋወጥና ፡ እንሞክረው ፤ የማንኛችን ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንረዳዋለን ፡ » አለችው ። እሱም ፡ ይኸማ ፡ ከሆነ ፡ መልካም ፡ ነዋ ፡ በማን ፡ ዕድሌ ፡ እጥላ ፡ ተቀምጬ ፡ ፀሐይ ፡ ሳይነካኝ ፡ ከቤት ፡ አንቺ ፡ የምትሠሪውን ፡ ብሠራ ፡ ሊያውከኝ ፡ ነው ? ቀላጅ ፡ በዪ ፡ ሂጅና ፡ የኔን ፡ ድካም ፡ ከበሬዎቹ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ የሞፈሩንና ፡ የቀምበሩን ፡ አያዝ ፡ ሞክሪው ፡ አላት ።

ሚስቱም ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ፈቃዱ ፡ ነው ። የቤቱን ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ተረከበኝ ፡ ብቻ ፡ እኔ ፡ እሠራው ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይጐድልብህ ፡ ጥዋት ፡ በማለዳ ፡ ተነሥተህ ፤ ውሃ ፡ ቀድተህ ፤ ቤት ፡ ጠርገህ ፤ በረት ፡ ከፍተህ ፤ ላሞችን ፡ ከጥጆች ፡ አገናኝተህ ፤ ወተት ፡ አሳልበህ ፤ ከብቶቹን ፡ ሣር ፡ ወዳለበት ፡ አሰማርተህ ፤ በኋ ፡ ሰዓት ፡ ምሳ ፡ አዘጋጅተህ ፡ በማርስበት ፡ ቦታ ፡ ይዘህልኝ ፡ እንድት መጣ ፡ ይሁን ፡ ብላ ፡ ነገረችው ። ባሏም ፡ አንቺም ፡ እኔ ፡ እንደም ሠራው ፡ ሞፈር ፡ ቀንበር ፡ ተሸክመሽ ፡ በሬ ፡ ጠምደሽ ፡ እንድታ ርሺ ፡ ይሁን ፡ ካንቺ ፡ ወገን ፡ ይሁንልሽ ፡ እንጂ ፤ ከኔ ፡ ወገንስ ፡ ያንቺ ፡ ሥራ ፡ አያውከኝም ፡ ብሏት ፡ ይህንን ፡ ተነጋግረው ፡ ውለ ታቸውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፤ በየሥራቸው ፡ ሄዱ ።

ሚስቱ ፡ ሞፈር ፡ ቀምበሩን ፡ ተሸክማ ፤ በሬዎቹን ፡ እየነዳች ፡ ከእርሻ ፡ ቦታ ፡ ሄዳ ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ገበሬ ፡ በትክክል ፡ ጠምዳ ፡ መሣሪያውን ፡ አስማምታ ፡ ሥራውን ፡ ጀመረች ። ባሏም ፡ የቤት ፡ ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ ውሃ ፡ ቀድቶ ፡ ቤት ፡ ከጠረገ ፡ በኋላ ፡ ወደ፡ በረት ፡ ሄዶ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፤ ላም ፡ አገናኝቶ ፤ ወተት ፡ አልቦ ፡ ሲመ ለስ ፤ የበረቱን ፡ በር ፡ ሳይዘጋው ፡ ቀርቶ ፡ ኖሮ ፤ ከብቶች ፡ ከቡቃያ፤ ፍየሎች ፡ ከጐመን ፡ ገብተው ፡ ብዙ ፡ ጥፋት ፡ አጠፉበት ። እሱም ፡ ወተቱን ፡ አልቦ ፡ ከቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ሥጋ ፡ ለመቀቀል ፤ ቁራርጦ ከእሳት ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ጥዶ ፡ ወተቱን ፡ ከጉርና ፡ እገለብጣለሁ ፡ ሲል ፤ ከጎረቤት ፡ ሰው ፡ ሲጣራ ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። ብቅ ፡ ብሎ ፡ ቢመ ለከት ፤ የበረቱ ፡ ከብቶች ፡ ሁሉ ፡ በየእህሉና ፡ በየአታክልቱ ፡ ተሰ ማርተው ፡ ብቻውን ፡ ቢሮጥ ፤ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ ቢቅበዘበዝ ፡ ማን፡ ይርዳው ? ብዙ ፡ ጥፋት ፡ ካጠፉበት ፡ በኋላ ፡ በጩኸት ፡ ብዛት ፤ በጎረቤት ፡ ብርታት ፡ ተሰብስበው ፡ ከበረት ፡ ገቡለት ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከቤት ፡ ቢገባ ፤ ሥጋውን ፡ ውሾች ፡ በልተ ውት ፡ ወተቱን ፡ ድመቶች ፡ ደፍተውት ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ የተጣደው ውሃ ፡ ፈልቶ ፡ እሳቱን ፡ አጥፍቶበት ፡ አገኘው ። በንዴት ፡ ላይ ፡ ንዴት ፤ በድካም ፡ ላይ ፡ ድካም ፡ ሆነበት ። አያይዞ ፡ ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ የማይቻለው ፡ በመሆኑ ፤ ከብቶችንም ፡ ከበረት ፡ እን ዳጎረ ፤ እጁን ፡ አጣምሮ ፡ ውሎ ፡ ቆያት ። ባለቤቲቷም ፡ በሚገባ ፡ ስትሠራ ፡ ውላ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሳይጐድልባት ፡ መሣሪያዋን ፡ ይዛ ፡ በሬዎችን ፡ እየነዳች ፡ በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋልህ

ምነው ፡ ምሳዬን ፡ ሳታመጣልኝ ፡ ቀረህ ፤ አንተስ ፡ ምን ፡ በልተህ ፡ ዋልህ ፡ አለችው ። እሱም ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሥቶ ፡ ማሪኝ ፡ ድካ ምሽን ፡ አየሁት ፡ ተረታሁ ፡ እኔ ፡ ቀላል ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፤ ለካስ ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሐተታ ፡ ብዙ ፡ ኖርዋል ፡ ብሎ ፡ ምሕረት ፡ ጠየቃት ።

እሷም ፡ ያታክልቷን ፡ መበላት ፤ የቤቷን ፡ መበላሸት ፤ የከ ብቶችን ፡ በበረት ፡ ታጉረው ፡ ጦም ፡ መዋል ፡ ከተረዳች ፡ በኋላ ፤ ሳትመረርና ፡ ሳትበሳጭ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሥራ ፡ ጀምራ ፡ ለባሏና ፡ ለእሷ ፡ ምግባቸውን ፡ አሰናድታ ፤ ለከብቶች ፡ ሣር ፡ ገፈራ ፡ ሰጥታ ፤ ሥራዋን ፡ ከወነች ። በማግስቱ ፡ ሁለቱም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ወንዱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሥራው ፡ ሴቲቱም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሥራዋ ፡ ተመለሱ ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምረው ፡ ሁለቱም ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እየተረዳዱ ፡ ያለ ፡ መመረር ፡ በትዕግሥት ፡ ዕድሜያ ቸውን ፡ ፈጸሙ ።

ልጆች ፤ የማይገባችሁንና ፡ የማትችሉትን ፡ ሥራ ፡ እንሠራ ለን ፡ አትበሉ ። ወደ ፡ ማጥፋት ፡ እንዳትደርሱ ፤ በተረፈ ፡ የሴቶች ፡ ሥራ ፡ ድካም ፡ እንዳለበት ፡ ሳይመረምር ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ በሥ ራዋ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ተወዳደረው ፡ ሰው ፡ ትሆናላችሁ ።

ምሳሌ ፤ ባልና ፡ ሚስት ፡ ፍትሕና ፡ መንግሥት ፤ ምንም ፡ ሴት ፡ ብታውቅ ፡ በወንድ ፡ ያልቅ ። ዕንጀራ ፡ ያለ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ያለሴት ፡ ከብት ፡ ያለ ፡ በረት ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይደጋገፉ ፡ ኖሯል ?
፪ኛ ፤ የወንዱን ፡ ገበሬ ፡ ሥራ ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።
፫ኛ ፤ የሴቷንም ፡ ጭምር ?
፬ኛ ፤ በመጨረሻ ፡ ምን ፡ ሆነ ?
፭ኛ ፤ በየምግባራቸው ፡ ተመለሱን ?
፮ኛ ፤ ይህ ፡ ከምን ፡ ምሳሌ ፡ ያደርሳል ?

ልጆች ።

ልጆች ፡ ፍቅርን ፡ ተከተሏት ፡ ብለው ፡ መምህራንና ፡ መጻሕፍት ፡ ቢመክሯችሁ ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ደራሽ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ ከሌላ ፡ ባሕርይ ፡ አንቅታችሁ ፡ አምጡ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። የልጅነት ፡ ባሕርያችሁን ፡ ጥበብና ፡ ትምህርትን ፡ ስትጨምሩበት ፡ አትለውጡት ፡ ማለት ፡ ነው ።

በተወለዳችሁ ፡ በአንድ ፡ በሁለትና ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ የወጣ ፡ የወረደውን ፤ ያለፈ ፡ ያገደመውን ፡ ሁሉ ፤ ወንዱን ፡ አበ ፤ ሴቷን ፡ እመ ፡ እያላችሁ ፤ ወንዶችን ፡ ትልቆችን ፡ አባታችን ፡ ትንሹን ፡ ወንድማችን ፤ ሴቶችንም ፡ ትልቋን ፡ እናታችን ፤ ትንሽዋን ፡ እኅታችን ፡ እያላችሁ ፡ ታድጋላችሁ ። ካደጋችሁም ፡ በኋላ ፡ ዘመድና ፡ ባዕድ ፡ ለይታችሁ ፡ ለዘመዳችሁ ፡ ታደላላችሁ ። ይህ ፡ ለፍቅር ፡ መንገዱ ፡ አይደለም ። አባትና ፡ እናት ፡ ወንድምና ፡ እኅትም ፡ የግድ ፡ ይወደዳሉ ፤ አባት ፡ እናት ፡ ፊትም ፡ በማር ፡ በወተት ፡ ያሳድጋሉ ። ኋላም ፡ ርስት ፡ ያወርሳሉ ። ወንድምና ፡ እኅትም ፡ የሥጋ ፡ ቁራጭ ፡ ያጥንትም ፡ ፍላጭ ፡ ናቸው ፤ ከአካላቱ ፡ አንዱን ፡ የሚወድ ፡ አንዱን ፡ የሚጠላ ፡ የለም ።

አሁንም ፡ ጥበብ ፡ የምታሳድጋችሁና ፡ የምታጐለምሳችሁ ፡ ልጆች ፡ በእውነት ፡ ፍቅርን ፡ ስትከታተሏት ፡ በፊት ፡ እንደተናገርነው ፡ የሕጻንነት ፡ ባሕሪያችሁን ፡ ሳትለውጡ ፡ ባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ነጭ ፡ ጥቁር ፡ ድኽ ፤ ሀብታም ፡ ሳትለዩ ፡ ሁሉን ፡ መውደድ ፡ ነው ። ካባት ፡ ከናታችሁ ፡ ቤት ፡ መጥታችሁ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ለመሄድ መንገድ ፡ በጀመራችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወሬና ፡ ጨዋታ ፡ አታብዙ ። ብዙ ፡ ቢያወጉ ፡ ይዘነጉ ፡ ብዙ ፡ ቢተቹ ፡ ይሰለቹ ፡ እንዲሉ ፡ ወሬ ፡ ከበዛ ፡ ዘንድ ፡ የተናገሩት ፡ ተረስቶ ፡ ከምን ፡ ተነሥተን ፡ ከዚህ ፡ ደረስን ፡ ያሰኛልና ። እናንተም ፡ በመንገድ ፡ ጨዋታ ፡ የለመዳችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትምህርትና ፡ ጥበብ ፡ የተመላ ፡ ልባችሁ ፡ ከምላቱ ፡ ተወስኖ ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ይመሰጣል ። ዘመድ ፡ በሩቅ ፡ ሰላምታ ፡ ቢሰጣችሁ ፡ አንገትን ፡ ዘንበል ፡ አድርጎ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ቀርቦ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ሲል ፡ ባጭሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋልህ ፡ ብሎ ፡ የሰላምታ ፡ መልስ ፡ ሰጥቶ ፡ ደኅና ፡

ሁን ፡ ለትምህርት ፡ ቸኩለናል ፡ ማለት ፡ ነው ።
ሲረዝም ፡ ይጠር ፡ ሲሰበር ፡ ይሠንጠር ፡ እንዲሉ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ከፍቅርስ ፡ ምን ፡ ይገኝበታል ?
፫ኛ ፤ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፬ኛ ፤ የሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕርዩ ፡ ስንት ፡ ነው ?
፭ኛ ፤ ዝንጋታ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?

ስለ ፡ ሦስት ፡ ሌቦች ።

በአንድ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ በእህሉ ፤ በላሙ ፡ በበሬው ፡ በግመሉ ፡ በፍየሉ ፡ በበጉ ፡ በከብቱ ፡ በማናቸውም ፡ ሁሉ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ከበርቴ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ስንኳንስ ፡ ከሀብታም ፡ ከድሃም ፡ ቢሆን ፡ ሌባ ፡ መስረቅ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ሌቦች ፡ ባንድነት ፡ ተማክረው ፡ ሌት ፡ ከቤት ፡ ገብተው ፡ ከከብቱና ፡ ከገንዘቡ ፡ ሰርቀው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ በረሃ ፡ ገቡ ።

ከበረሃም ፡ ሁነው ፡ ሁለቱ ፡ ሌቦች ፡ ሦስተኛውን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በስውር ፡ ምግብ ፡ ገዝቶ ፡ አምጥቶላቸው ፡ እንዲበሉ ፡ ልከውት ፡ ሄደ ። ከሄደም ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ከበረሃ ፡ የቀሩት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተመካከሩ ። ሦስተኛውን ፡ ጓደኛቸንን ፡ ሳንጨምር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ብንካፈለው ፡ ብዙ ፡ ይጠቅመናል ። ይኸውም ፡ ባልጀራችን ፡ ሲመጣ ፡ ተደብቀን ፡ እንግደለው ፡ ብለው ፡ ሐሳባቸውን ፡ ጨረሱ ።

ያኛውም ፡ ወደ ፡ ላኩት ፡ ስፍራ ፡ ሲሄድ ፡ ለራሱ ፡ እንዲህ ፡ ያስብ ፡ ነበር ፤ መቼም ፡ ፋንታዬን ፡ በልቼ ፡ ነውና ፡ የምመለስ ፡ እነሱን ፡ በዚህ ፡ በምወስድላቸው ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ መርዝ ፡ ገዝቼና ፡ ነሳንሼ ፡ ፈጅቻቸው ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለብቻዬ ፡ እወርሳለሁ ፡ ብሎ ፡ እንዳሰበው ፡ አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ከነሱም ፡ ዘንድ ፡ ሊደርስ ፡

ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ እንደ ፡ ተማከሩት ፡ ተደብቀው ፡ ተኩሰው ፡ ገደ
ሉት ። ፈጥነውም ፡ ሄደው ፡ ምግቡን ፡ በልተው ፡ ሩብ ፡ ሰዓት ፡
ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ እየተንጨፈረሩ ፡ ሞቱ ። እነዚያም ፡ ለሁለት ፤
እሱም ፡ ለራሱ ፡ ሲያስብ ፡ ምንም ፡ ሳያገኙ ፡ ጠፍተው ፡ የሁሉም ፡
ሌቦች ፡ ሬሳ ፡ ከዚያው ፡ ተገኘ ። የተሰረቀውም ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡
ሳንቲም ፡ እንኳ ፡ ሳይነሣለት ፡ አብሮዋቸው ፡ ባንድነት ፡ ተገኝቶ ፡
ለዋና ፡ ባለቤቱ ፡ ነጻ ፡ ገንዘቡ ፡ ተመለሰለት ፡ ይባላል ።

የሌባ ፡ ትርፉ ፡ ጥፋቱ ፡ ነው ። የሰው ፡ ገንዘብ ፡ በከንቱ ፡ ቢሄ
ድ ፡ አለመጥቀሙን ፡ እኒህ ፡ ምሳሌዎች ፡ ያስረዱናል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከበርቴው ፡ ምን ፡ ምን ፡ ኖሮታል ?
፪ ፤ ሌቦች ፡ ምን ፡ አደረጉበት ?
፫ ፤ ሰብረውስ ፡ ወዴት ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ?
፬ ፤ ወደ ፡ ከተማ ፡ የተላከው ፡ ምን ፡ ተንኰል ፡ አሰበ ?
፭ ፤ አስቦስ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ መጣ ?
፮ ፤ ከሰፈርስ ፡ የቆዩት ፡ ምን ፡ ዶለቱ ?
፯ ፤ ጓደኛቸውንስ ፡ ምን ፡ አደረጉት ?
፰ ፤ በመጨረሻው ፡ የቀሩትን ፡ ምን ፡ አገኛቸው ?

የልጅ ፡ ደግነት ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ። መጀመሪያ ፡ የወለደ
ውን ፡ ወንዱን ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ ይወደው ፡ ነበር ። ከፍቅሩ ፡ ጽናት ፡
የተነሣ ፡ ይከሳብኛል ፡ ይጠቁርብኛል ፡ እንዳለለት ፡ ያድራል ፡ እያ
ለ ፡ ሳያስተምረውና ፡ ሳይቀጣው ፡ በቧልት ፡ በጨዋታ ፡ አሳደ
ገው ። ከወንድ ፡ ልጁ ፡ ቀጥላ ፡ የተወለደችውን ፡ ሴቲቱን ፡ ልጅ ፡
ግን ፡ በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ቀጥቶ ፡ አሳደጋት ።

ሁለቱም ፡ ልጆች ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሲደርሱ ፡ ያለ ፡ ገንዘ
ቡን ፡ ጨርሶ ፡ በሚገባ ፡ አድርጎ ፡ ደግሶ ፡ ለወንዱ ፡ ሚስት ፤ ለሴ

ቲቱ ፡ ባል ፡ አጋባቸው ። ሴቲቱ ፡ ልጅ ፡ በሕግ ፡ ጸንታ ፤ ባሏን ፡ አክ
ብራ ፤ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዛ ፡ በተዳረችበት ፡ አገር ፡ ተቀመጠች ።
ወንዱ ፡ ባገባ ፡ በመንፈቁ ፡ ሚስቱን ፡ ፈቶ ፡ አገሩን ፡ ጥሎ ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ለጌታ ፡ አደረ ። በሄደበት ፡ አገርም ፡ ብዙ ፡ ገን
ዘብና ፡ ሹመት ፡ አገኘ ። አባት ፡ እናቱ ፡ ግን ፡ ለሥራ ፡ ያልደረሱ ፤
ለመብል ፡ ያላነሱ ፡ ሕጻናት ፡ ያሳድጋሉና ፡ በጣም ፡ ደኸዩ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሴቲቱ ፡ ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ነበረችና ፡
ባሏን ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤ እኔ ፡ የምወልድበት ፡ ቀን ፡ ደረሰ ፤
በቤታችን ፡ አንድ ፡ ቁና ፡ ዱቄት ፡ እንኳ ፡ የለም ፤ ወልጄ ፡ የተኛሁ ፡
እንደሆን ፡ ምን ፡ እቀምሳለሁ ፤ ትልቁ ፡ ልጄ ፡ ተሾሞ ፡ ባለብዙ ፡
ገንዘብ ፡ ሆኗል ፡ አሉ ። ሄደህ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጥህ ፡ አምጣልኝ ፡
አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ሄዶ ፡ ከልጁ ፡ ቤት ፡ ሲደርስ ፡ ንገ
ሩልኝ ፡ አለ ፤ ወዲያው ፡ አሽከሮቹ ፡ ገብተው ፡ አባትዎ ፡ መጥተ
ዋል ፡ አሉት ፤ ጉዳይ ፡ ይዣለሁና ፡ ይቆይ ፡ አለ ፤ ወዲያው ፡ ረስ
ቶት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ እውጭ ፡ አድሮ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በመል
ክት ፡ ብዛት ፡ ተገናኝቶ ፤ እኔ ፡ ደኸየሁ ፤ ከእጄ ፡ ገንዘብ ፡ አጣሁ ፤
እናትህም ፡ ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ናትና ፡ መውለጃዋ ፡ ደርሷል ፤ ጥቂት ፡
ገንዘብ ፡ ትሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡ አለው ።

እሱም ፡ አሽከሮቼንና ፡ ገረዶቼን ፡ የማለብስበት ፡ አጥቻለሁ ፡
ምን ፡ ላድርግልህ ፡ አለውና ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ሚስቱ ፡
ልጄ ፡ ገንዘብ ፡ ይልክልኛል ፡ ብላ ፡ ትጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡
ደደረሰ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ አለችው ። ምንም ፡ አልሰጠኝ ፡
ባዶ ፡ እጄን ፡ ሰደደኝ ፡ አላት ። ደንግጣ ፡ አዝና ፡ እስኪ ፡ ደግሞ ፡
ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ ልጄ ፡ ሂድልኝ ፡ አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡
ሄደ ፤ ከልጁ ፡ ቤት ፡ ሲደርስ ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ቢል ፡ ልጁ ፡
ድምጡን ፡ ለይታ ፡ በፍጥነት ፡ ወጥታ ፡ ዕልል ፡ እያለች ፡ ከጫማው
ወደቀች ፤ ጫማውን ፡ ትከሻውን ፡ ስማ ፡ በደስታ ፡ ተቀብላ ፡ ወደ ፡
ቤት ፡ ይዛው ፡ ገባችና ፡ በራዋን ፡ አሳርዳ ፡ እየመገበች ፡ ስምንት ፡
ቀን ፡ አሰንብታ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ በቅሎ ፡ ላምና ፡ በሬ ፡ የሚበቃ
ውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥታ ፡ አሰናበተችው ።

እሱም ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ከብቶቹን ፡ እየነዳ ፡ ከቤቱ ፡ አጠ
ገብ ፡ ሲደርስ ፡ ከጎረቤቱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘና ፡ እንዴት ፡ ዋልህ
ማነው ፡ እንደዚህ ፡ ሸልሞ ፡ የሰደደህ ፡ አለው ፤ እሱም ፡ ሴቲቱ ፡

ልጄ ፡ ደስ ፡ አሰኝታ ፡ ሰደደችኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ከቤትህም ፡ ሚስትህ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተገላግላ ፡ ደስታ ፡ ሆኗል ፡ አለው ። ወንድ ወለደች ፡ አልኸኝ ፡ እቤቴም ፡ አልገባ ፡ ከብቶቹን ፡ መልሱልኝ ፡ ወዳጄን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ እንዳትወልድልኝ ፡ ጠላቴን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ብሎ ፡ አገር ፡ ጥሎ ፡ ለመሄድ ፡ ቢነሣ ፤ ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ገላግሎ ፡ የወለደው ፡ ልጅ ፡ ለጋላ ፡ ተሰጥቶ ፡ እቤቱ ፡ ገባ ፡ ይባላል።

ልጆች ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የወለደውን ፡ ሕጻን ፡ የጠላበት ፡ ምክንያት ፡ ታላቁ ፡ ልጁን ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ በቧልታ ፡ በጨዋታ ፡ ስላሳደገው ፤ ወላጅ ፡ አባቱን ፡ አስቀይሞ ፡ መለሰው ። ሴቲቱ ፡ ልጅ ፡ በትምህርት ፡ ስላደገች ፤ ደስ ፡ አሰኝታ ፡ ሰደደችው ። ይህ ነን ፡ ነገር ፡ አመዛዝኖ ፡ ነውና ፡ የተናገረው ፡ እውነት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ በመወለዱ ፡ ጠልቶ ፡ አልነበረም ። አሁንም ፡ እንደዚህ ፡ እንዳትሆኑ ፡ አገራችሁን ፡ አፍቃሪ ፡ አባት ፡ እናታችሁን ፡ አክባሪ ፡ እንድትሆኑ ፡ ለትምህርት ፡ የተዘጋጃችሁ ፡ ሁኑ ፤ ጠንቅቃችሁ ፡ መርምሩ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ቧልት ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?

፪ኛ ፤ አባት ፡ ወደ ፡ ወንድ ፡ ልጁ ፡ ቤት ፡ ሂዶ ፡ በምን ፡ ተመለሰ ?

፫ኛ ፤ የሴቷ ፡ ልጁን ፡ አቀባበል ፡ ተናገር ።

፬ኛ ፤ አባት ፡ ከቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ ምን ፡ የምሥራች ፡ ሰማ ? ምንስ ፡ ተናገረ ?

፭ኛ ፤ ያገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ምን ፡ አደረጉ ?

አባትና ፡ አባካኝ ፡ ልጅ ።

አንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ታናሹ ፡ ላባቱ ፡ አለው ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ መን ፈቴ ፡ መራኝ ፤ ከከብቱና ፡ ከገንዘቡ ፡ ድርሻዬን ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።

እሱም ፡ በተቻለው ፡ መከረው ። ልጁም ፡ እንቢ ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከብርና ፡ ከወርቁ ፡ ከከብቱም ፡ መሐከል ፡ ታላቅ ፡ ወንድ ሙንና ፡ እሱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አቁሞ ፡ በል ፡ ልጄ ፡ የመረጥኸውን ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ልጁም ፡ ለዐይኑ ፡ ጐልቶ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ፤ ይዞም ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደ ። ከሄደበት ፡ አገር ፡ ከብቱን ፡ ሁሉ ፡ በሣቅ ፡ በዋዛ ፡ በፈዛዛ ፡ ጨርሶ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ቀረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ መብላትን ፡ ቢፈልግ ፡ እሪያ ፡ መጠበቅን ፡ ብቻ ፡ አገኘ ። ከዚያም ፡ ውስጥ ፡ ለምግቡ ፡ የሚበቃውን ፡ እንኳን ፡ የሚሰጠው ፡ አላገኘም ። በአገሩም ፡ ውስጥ ፡ ረኃብ ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ አዘነ ፤ ልቡናውም ፡ ተመልሶ ፡ የአባቴ ፡ አገልጋዮች ፡ ስንት ፡ ናቸው ። እነሱ ፡ እንጀራ ፡ ተርፏቸው ፡ ነው ፡ የሚኖሩት ፡ እኔ ፡ በረኃብ ፡ ከዚህ ፡ እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ወደዚያውም ፡ ልነሣና ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ ልሂድ ፤ ልበለውም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በሰማይ ፡ ፈጣሪዬን ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ አባቴን ፡ በደልሁ ፤ ልጅህም ፡ እባል ፡ ዘንድ ፡ አይገባኝም ። ከባሮችህ ፡ እንዳንዱ ፡ አድርገኝ ፡ እንጂ ፤ ሄዶም ፡ እንደዚሁ ፡ ብሎ ፡ ካባቱም ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። አባቱም ፡ አይቶት ፡ አለቀሰ ፤ ካንገቱም ፡ ላይ ፡ ተጠመጠመ ፤ ሳመውም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ አሽከሮቹን ፡ ጠራ ፤ መልካም ፡ ልብስና ፡ ጫማ ፡ ቀለበትም ፡ አምጡለት ፡ ብሎ ፡ አስመጣለት ፤ አለበሰውም ፤ ፍሪዳም ፡ ታረደ ። አባቱም ፡ አሽከሮቹን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አቁሞ ፡ ዛሬ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ይህ ፡ ልጄ ፡ ከሞት ፡ አገር ፡ መጥቶዋልና ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ሲጫወቱ ፡ በዓልም ፡ ሲደረግ ፡ ትልቁ ፡ ልጁ ፡ ከመንገድ ፡ ሄዶ ፡ ነበርና ፡ መጣ ። ከውጭም ፡ ቆሞ ፡ ቢያዳምጥ ፡ የልልታና ፡ የዘፈን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤ ከነ ረቤትም ፡ ሄዶ ፤ ዛሬ ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ በዓል ፡ አለ ? ዘፈን ፡ እሰማለሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። ትንሹ ፡ ወንድምህ ፡ መጥቶ ፡ በዓል ፡ ሆኖ ፡ ሰነበተ ፡ አሉት ። እንግዲያስ ፡ ምኑን ፡ ገባሁት ፡ ተመልሼ ፡ ቆርበቴን ፡ ጠቅልዬ ፡ ሥንቄን ፡ ይዤ ፡ ልጥፋ ፡ አለ ።

አባቱም ፡ ሰምቶ ፡ ከቤት ፡ ወጣ ። አለውም ፡ ልጄ ፡ እባክህ ፡ ግባልኝ ፤ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፤ ልጁም ፡ መለሰ ፤ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ አገለገልሁህ ፤ ፈቃድህንም ፡ አልጣስሁም ። ነገር ፡ ግን ፡

አንዲት ፡ የፍየል ፡ ግልግል ፡ እንኳን ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ከባልንጀሮቼ ፡ ጋራ ፡ ደስታ ፡ አላደረግሁም ። ይህ ፡ ግን ፡ ከገንዘቡ ፡ ከፍተኛውን ፤ ከመንጋውም ፡ ብዙውን ፡ ከፍለህ ፡ ሰጥተኸው ፡ ያነን ፡ ሁሉ ፡ ወስዶ ፡ በሣቅ ፡ በዋዛ ፡ በፈዛዛ ፡ ያጠፋ ፡ ልጅህ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የተረፈውን ፡ ሊያጠፋ ፡ ቢመጣ ፡ ሠንጋ ፡ አረድህለት ፡ ብሎ ፡ አባቱን ፡ ወቀሰው ።

አባቱም ፡ ተጨነቀና ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይቅርታህን ፡ አድርግ ልኝ ፤ ይቅር ፡ ካላሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ አይልምና ፤ አንተ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነህ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ከሞት ፡ አገር ፡ ነው ፡ የመጣው ፤ ከኔም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ያንተ ፡ ነው ፤ አሁንም ፡ ከወንድምህ ፡ ታርቀህ ፡ ደስታችንን ፡ እንፈጽም ፤ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ምሕረቱም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ክፉ ፡ ለሠራብህ ፡ ደግ ፡ ሥራለት ፡ ብሏል ፤ ይህንንም ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ያባቱን ፡ ምክር ፡ ሰምቶ ፡ ተያይዘው ፡ ከቤት ፡ ገቡ ። ከወንድሙም ፡ ጋራ ፡ ዐይን ፡ ላይን ፡ በተያዩ ፡ ጊዜ ፡ ይልቁንም ፡ ከአባቱ ፡ ይበልጥ፡ አዝኖ ፡ ተስማምተው ፡ በዓላቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ምሳሌ ፤ ከአባት ፡ ቃል ፡ መውጣት ፡ ያደርሳል ፡ ከሞት ። ሰጥቶ ፡ ከእጁ ፤ ለመነ ፡ ከደጁ ። ጀንበር ፡ ሳለ ፡ ሩጥ ፤ አባት ፡ ሳለ ፡ አጊጥ ። የዘመድ ፡ ጥል ፤ የሥጋ ፡ ትል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የአባትን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል ?
፪ኛ ፤ የአባትንስ ፡ ፈቃድ ፡ ማፍረስ ፡ ምን ፡ ይጐዳል ?
፫ኛ ፤ ከማንዘራሽና ፡ ከአታላዮች ፡ ጋራ ፡ መዋል ፡ ከምን፡ ያደርሳል ?

የዋህ ፡ ባላገር ።

አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ከመኳንንቱና ፡ ከባለሟሎቹ ፡ ጋራ ፡ ለሽርሽር ፡ ወዲያውም ፡ ለአደን ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ ከተ

ከታዮቹ ፡ መሐከል ፡ ላደን ፡ ርቆ ፡ በመሄዱ ፤ ከመኳንንቱ ፡ ስለ ፡ ተለያየ ፤ ብቻውን ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲመለስ ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ከጥላ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ ለንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ አንተ ፡ ሰው ፡ እባክህ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ንጉሥ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ለአደን ፡ ብለው ፡ ሄደዋልና ፡ የሚመለሱበትን ፡ መንገድና ፡ ሰዓት ፡ አስታውቀኝ ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለህ ፡ የምትነግረው ፡ ቢለው ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የንጉሥን ፡ መልክ ፡ ስላላየሁ ፡ ባልቀርብ ፡ እንኳ ፡ በሩቁ ፡ ዐይናቸውን ፡ ልየው ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለው ።

ንጉሡም ፡ ባነጋገሩ ፡ ተደንቆ ፡ ና ፡ ከፈረሴ ፡ ላይ ፡ ተፈናጠጥ ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡ ንጉሡን ፡ አሳይሃለሁ ፡ ብሎት ፡ ተፈናጠው ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ ባላገሩ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ እረ ፡ በል ፡ ጌታው ፡ አንተስ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ትወስደኛለህ ፤ ከቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ታገባኛለህ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ በምን ፡ ምልክት ፡ ዐውቀዋለሁ ፡ አለው ። ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ የምታውቀው ፡ ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ባርኔጣውን ፡ እያወለቀ ፡ እጅ ፡ ሲነሣው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ባርኔጣውን ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ እንዳደረገ ፡ የሚገባውን ፡ ክብርና ፡ ሰላምታ ፡ ሲቀበል ፡ በማየትህ ፡ ነው ፡ አለው ።

ይህን ፡ ተነጋግረው ፡ ወዲያው ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ከፊት ፡ በር ፡ ጀምሮ ፡ እስከልፍኝ ፡ ደጃፍ ፡ ድረስ ፡ የንጉሥን ፡ መመለስ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ቆሞ ፡ የሚጠባበቀው ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ያልታወቀ ፡ ሰው ፡ በፈረስ ፡ አፈናጠ ፡ ሲመጣ ፡ አይቶ ፡ ባርኔጣ ፡ እያወረደ ፡ እጅ ፡ እየነሣ ፡ ሲያሳልፈው ፡ ባላገሩ ፡ እየተደነቀ ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ መድረክ ፡ ድረስ ፡ ደረሱ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ እህ ፡ ባላገር ፡ አሁንሳ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ አላወቅኸውምን ፡ አለው ። ባላገሩም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ በጣም ፡ ተደንቄያለሁ ፤ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ባርኔጣ ፡ እያወረደ ፡ እጅ ፡ ሲነሣን ፡ እያየሁ ፡ ሁለታችን ፡ ብቻ ፡ ነን ፡ ባርኔጣ ፡ ያላወረድን ፤ እንግዲህ ፡ ከኔና ፡ ካንተ ፡ አንዳችን ፡ ንጉሥ ፡ እንሆናለን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። በየዋህነቱና ፡ በገርነቱ ፡ ተደንቆ ፡ ለኑሮው ፡ የሚበቃውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ ንጉሡ ፡ ሰደደው ፡ ይባላል ።

ምክር ፤ ልጆች ፤ ይህ ፡ ባላገር ፡ ንጉሡን ፡ ወዶ ፡ ያላሰበውን ፡

ገንዘብ ፡ አገኝ ። እናንተም ፡ በልባችሁ ፡ የዋህ ፤ በሰውነታችሁ ፡ ብልኅ ፡ ሁናችሁ ፡ አገራችሁንና ፡ መንግሥታችሁን ፡ ብትወዱ ፡ ዋጋችሁ ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፡ ገበሬ ፡ በንጉሥ ፡ ደብተራ ፡ በጳጳስ ፡ መበለት ፡ በቄስ ፡ መመቅኘት ፡ አይገባም ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የዋህ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ፡ ባላገሩ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ?
፫ኛ ፤ ባላገሩ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ?
፬ኛ ፤ ባላገሩስ ፡ ምን ፡ መለሰለት ?
፭ኛ ፤ በየዋህነቱ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አገኘበት ?

ዶሮና ፡ ቀበሮ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንዲት ፡ ቀበሮ ፡ ርቧት ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ ስታ ኰተኩት ፡ ከመንደር ፡ አጠገብ ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዶሮ ፡ ከዛፍ ፡ ተሰቅሎ ፡ አገኘችና ፡ አንተ ፡ ዶሮ ፡ እንዴት ፡ ዋልህ ፡ አለችው ። እሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ብሎ ፡ ሰላምታ ፡ ከመለሰላት ፡ በኋላ ፡ ምነው ፡ ወንድሜ ፡ ከማኅበር ፡ ተለይተህ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ መቅረትህ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ ደንግጦ ፡ ተለይቼ ፡ የቀረሁት ፡ ከምኑ ፡ ነው ? አላት ። እርስዋም ፡ ያልሰማው ፡ መጣ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ብላ ፡ የሚታለልላት ፡ መስሏት ፡ ተንኰልዋን ፡ እውነት ፡ እያስመሰለች ፡ ትለቀው ፡ ጀመረች ፤ ዛሬ ፡ እኮ ፡ እንስሳትና ፡ የዱር፡ አራዊት ፡ የሰማይ ፡ አዕዋፍም ፡ ተሐዋስያን ፡ የተባሉ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ሳይቀር ፡ ከሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ተሰብስበው ፡ የሰላምና ፡ የፍቅር ፡ ስምምነት ፡ ጉባኤ ፡ ተደርጎ ፡ ጉልበታሙ ፡ ደካማውን ፡ እንዳያጠቃ ፤

ሁሉም ፡ ተከባብሮ ፡ እንዲኖር ፡ ሥራት ፡ ተሠርቶ ፤ ተደንግጎ ፡ ተወሰኖ ፡ አንደኛው ፡ ማኅበረተኛ ፡ እኔ ፡ ነበርሁና ፡ ከዚያው ፡ ውዬ ፡ ይኸውና ፡ አሁን ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፡ አለችው ።

ያም ፡ ዶሮ ፡ ተንኰሏን ፡ ስላወቀባት ፡ ለካ ፡ ከዚህ ፡ ከኛ ፡ በላይ ፡ ካለው ፡ ስፍራ ፡ ወደኛ ፡ እየሮጡ ፡ ሲመጡ ፡ የማያቸው ፡ ውሾች ፡ አንዳች ፡ መልካም ፡ የምሥራች ፡ ሊነግሩኝ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ይምጡና ፡ እኔም ፡ ልውረድና ፡ ሁላችን ፡ ደስ ፡ ብሎን ፤ በዓሉን ፡ አክብረን ፡ እንውላለን፡ ብሎ ፤ የውሾቹን ፡ መምጣት ፡ ባወራላት ፡ ጊዜ ፡ እባብ ፡ ለባብ ፡ ይተያያሉ ፡ በካብ ፤ እንዲሉ ፡ በተንኰል ፡ ተንኰሏን ፡ ድል ፡ በነሣው ፡ ጊዜ ፡ ተወው ፡ ረስቼው ፡ ነው ፤ ዛሬስ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ አለብኝና ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ይሁንልኝ ፡ ብላ ፡ እየሮጠች ፡ እግሬ ፡ አውጭኝ ፡ እያለች ፡ ወደ ፡ ስፍራዋ ፡ ሄደች ።

ቀበሮ ፡ ያወራችለት ፡ የዕርቅ ፡ ወሬ ፡ እውነት ፡ እንዳልነበረ ፡ ዶሮውም ፡ ያወራላት ፡ የውሾቹ ፡ መምጣት ፡ ወሬ ፡ እውነት ፡ አልነበረምና ፡ ያ ፡ ዶሮ ፡ እየሣቀ ፡ እየተንከተከተ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

አሁንም ፡ ይህ ፡ ዶሮና ፡ ይህች ፡ ቀበሮ ፡ የሠሩት ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ነበረ ። ስለ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ያች ፡ ቀበሮ ፡ አዳሯ ፡ እያደነች ፡ የፍየል ፡ ግልገል ፡ እያነቀች ፡ በግ ፡ እየነጠቀች ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ምግብዋ ፡ ያንን ፡ ዶሮ ፡ አታላ ፡ የምትይዝበት ፡ ምክንያት ፡ መፈለጓ ፡ ስለ ፡ ትዳሯ ፡ የሚያስፈልጋት ፡ ነው ።

እውነት ፡ ነው ፡ ያም ፡ ዶሮ ፡ ከጠላት ፡ የሚያመልጥበትን ፡ መርምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ማድረጉ ፡ ሕይወቱን ፡ ስለ፡ መጠበቅ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው ።

ልጆች ፤ ይህች ፡ ቀበሮ ፡ ዶሮውን ፡ የምታጠፋበትን ፡ ምክንያት ፡ እየነገረች ፡ ብትፈታተነው ፤ ከሷ ፡ የሚበልጥ ፡ ተንኰል ፡ አምጥቶ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ መንሣቱ ፤ እናንተም ፡ ያልሆነ ፡ ምሳሌ ፡ እያመጣ ፡ ጥፋትን ፡ ከሚያስከትል ፡ ሰው ፡ ተጠንቀቁ ።

ምሳሌ ፤ ነገር ፡ እንዳፉ ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ ቅርንጫፉ ፤ ዶሮን ፡ ሲያታልሏት ፡ በመጫኛ ፡ ጣሏት ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ተንኰል ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ ምን ፡ ልዩነት ፡ አለው ?
፫ኛ ፤ ቀበሮ ፡ ለዶሮ ፡ ምን ፡ አለችው ?
፬ኛ ፤ ዶሮውስ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ምን ፡ መለሰላት ?
፭ኛ ፤ የቀበሮዋስ ፡ ተንኰል ፡ ለምን ፡ ኖሯል ?
፮ኛ ፤ የዚህን ፡ ምሳሌ ፡ ተናገር ።

እባብና ፡ ሃይማኖታዊ ፡ እስላም ።

ከሡልጣኑ ፡ ግቢ ፡ ዐውቆ ፡ ጥፋቱን ፤
እባብ ፡ ሸሽቶ ፡ ወጣ ፡ ሊያድን ፡ ሕይወቱን ።
የታዘዙ ፡ ጭፍሮች ፡ ፍለጋውን ፡ ይዘው ፤
ሊይዙት ፡ ነበረ ፡ በስተ ፡ ኋላው ፡ ደርሰው ።
ካንድ ፡ ጌታ ፡ ግቢ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡
በአላህ ፡ ስምና ፡ ነቢዩንም ፡ ጠርቶ ።
ሸሽገህ ፡ አድነኝ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ፤
ጌትዮው ፡ ከጓዳ ፡ ተደቢቅ ፡ አለው ።
እባቡም ፡ መለሰ ፡ ከሚስትህ ፡ ጠጉር ፡ ውስጥ ፤
ወዲያው ፡ ይይዙኛል ፡ ብገባም ፡ አላመልጥ ።
አሁንም ፡ አላህን ፡ ነቢዩን ፡ ጠርቼ ፤
መጣሁ ፡ ልትደብቀኝ ፡ ከልብህ ፡ ገብቼ ።
ይህንን ፡ ንግግር ፡ ሰውዬው ፡ ቢሰማ ፤
አውሬነቱ ፡ ቀፎት ፡ በልቡ ፡ አቅማማ ።
ስለ ፡ ነቢዩና ፡ ስለ ፡ አላህም ፡ ፈርቶ ፤
አፉን ፡ ከፈተለት ፡ ተሸሸገ ፡ ገብቶ ።
ፈላጊዎች ፡ መጡ ፡ እየተሯሯጡ ፤
የሡልጣኑን ፡ ጠላት ፡ አትደብቁ ፡ አምጡ ።
ተከታትለነዋል ፡ ከዚህ ፡ ከግቢህ ፡
የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ አሉት ፡ ወዮልህ ።

እኔ ፡ አላየሁትም ፡ ብሏቸው ፡ ባያምኑ ፤
ቤቱን ፡ በረበሩት ፡ አልቀረም ፡ ሣጥኑ ።
እባቡንም ፡ ቢያጡት ፡ ቀርበው ፡ ከዚህ ፡ ጌታ ፤
ስለ ፡ ድፍረታቸው ፡ ለምነው ፡ ይቅርታ ፤
ሄዱ ፡ ሊፈልጉ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ።
ወዳጇ ፡ እባብ ፡ ሆይ ፡ ጌትዮውም ፡ አለው ፤
ጠላቶችህ ፡ ሄዱ ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ ርቀው ፤
እንግዲህ ፡ ውጣልኝ ፡ ልቤን ፡ አስጨነቅኽው ።
እባቡም ፡ መለሰ ፡ እጅግ ፡ ሞኝ ፡ ነህ ፤
የእባብ ፡ ልጅ ፡ መሆኔ ፡ እንዴት ፡ ተሳተህ ፤
አንድ ፡ ጉርሻ ፡ ሳልይዝ ፡ የምሄድ ፡ መስሎህ ፤
ከልብህም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከሳምባህ ።
በዚህ ፡ በምላሹ ፡ ጌትዮው ፡ ደንግጦ ፤
ከኒህ ፡ ብልቶቼ ፡ አንዱማ ፡ ተቆርጦ ።
መሞቴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መትረፌስ ፡ ዘበት ፡ ነው ።
ወሮታዬን ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ከመለስኽው ፤
ጸሎቴን ፡ እስካደርግ ፡ ጊዜ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።
ይህንንስ ፡ ይሁን ፡ ስላለው ፡ ሄደና ፤
ካትክልቱ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ተናጸና ፤
ከሰውነቱም ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ኑዛዜ ፤
ስለ ፡ ብልጽግናው ፡ በዛበት ፡ ትካዜ ።
እንደ ፡ ቀረ ፡ አይቶ ፡ ክብሩና ፡ ተድላው ፤
እጅግ ፡ የመረረ ፡ ጎዘን ፡ ተሰማው ፤
የማይቀር ፡ ነውና ፡ እባብ ፡ ያሰበው ፤
የምታደርገውን ፡ በል ፡ አድርግ ፡ አለው ።
ገና ፡ ይኽ ፡ ቃሉ ፡ ካፉ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፤
አንድ ፡ ቀይ ፡ ጕልማሳ ፡ ተገልጦለት ፡ መጣ ።
ይህን ፡ ቅጠል ፡ ቍረጥ ፡ የአላህ ፡ ስሙን ፡ ጠርተህ ፤
ትድናለህ ፡ አለው ፡ ብትውጥ ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ።
አልተጠራጠረም ፡ ቅጠሉንም ፡ ዋጠው ።
እባቡም ፡ ደም ፡ ሆኖ ፡ ወዲያው ፡ አስታወከው ።
በሃይማኖት ፡ ጽናት ፡ ይኽ ፡ ሰው ፡ ሲድን ፤
ተንኰልን ፡ እንተው ፡ እንያዝ ፡ ጽድቅን ፤

በውነት ፡ አሸናፊ ፡ ተንኰል ፡ ቢመስል ፤
የጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ መጨረሻው ፡ ድል ።

ዮ. አ. ወ.

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ አባቡ ፡ ቍጥሩ ፤ ከማንኛቸው ፡ አውሬ ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ እስላሙ ፡ ከልቡ ፡ ውስጥ ፡ እባቡን ፡ ያስገባው ፡ የማንን ፡ ስም ፡ ቢጠራበት ፡ ነው ?
፫ኛ ፤ ወሮታ ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፬ኛ ፤ በመጨረሻ ፡ እባቡ ፡ ምን ፡ ሆነ ?

አዲስ ፡ ፍጥረት ።

አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ነበር ። ሰምተን ፡ የማናውቀው ፤
ከወገቡ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሁለት ፡ ሰው ።
ከወገቡ ፡ በታች ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ አካል ፤
መስሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ በባላ ፡ አምሳል ።
አንደኛው ፡ ሲያማርር ፡ ስለ ፡ ተፈጥሮው ፤
አምላኬ ፡ ተመስገን ፡ ይለዋል ፡ ሌላው ፤
እንደ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘጸጋም ፡ አንደኛው ፤
አታመስግን ፡ ብሎ ፡ ክሕደቱን ፡ አሰማው ።
ሁለት ፡ ሰው ፡ ተጣብቀን ፡ ጉዶች ፡ ተወልደናል ፤
ሕዝቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለትንግርት ፡ ያየናል ።
ኧረ ፡ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ እንዳይመጣብን ፤
ጢት ፡ ማታ ፡ አምላክን ፡ አለው ፡ የምትለምን ።
ሌላውም ፡ መለሰ ፡ ይህን ፡ አልሰማህም ፤
የባሰ ፡ ለማምጣት ፡ ለአምላክ ፡ አይገደውም ።
ይህን ፡ የሰበከው ፡ መጀመሪያ ፡ ሙቶ ፤
ከሐዲውም ፡ በድሜ ፡ ቆየ ፡ ተለይቶ ።
ምን ፡ ይመጣል ፡ ባዩ ፡ ሳይዘገይ ፡ ጥቂት ፤

ታቀፈ ፡ ሬሳውን ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ።
ወዲህ ፡ በክብደቱ ፡ ወዲህ ፡ በሽታው ፤
የዚህ ፡ የቆመ ፡ ሰው ፡ በዛ ፡ መከራው ።
አምላክን ፡ አናማር ፡ እጁ ፡ እንዳይቆጣ ፤
ይልቅስ ፡ እንበለው ፡ የባሰ ፡ አታምጣ ።

ጥ ያ ቄ ።

፭ኛ ፤ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ የተባለው ፡ ምን ፡ ልዩነት ፡ ቢኖረው ፡ ነው ?
፮ኛ ፤ ክሕደት ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፯ኛ ፤ የማማረር ፡ ትርፉ ፡ ምን ፡ ሆነ ?

ዝንጆሮ ።

አንዲት ፡ ዝንጆሮ ፡ ናት ፡ የምታስደንቀን ፤
ሥራዋን ፡ ስናስብ ፡ ዘዴኛ ፡ ነች ፡ ብለን ።
አንድ ፡ ቀን ፡ ስትሄድ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጫካ ፤
በመላው ፡ አካሏ ፡ ብዙ ፡ እሾህ ፡ ተሰካ ።
እንዳትቀመጥም ፡ ወይም ፡ እንዳትቆም ፤
ወግቶ ፡ አስጨንቋት ፡ ተጠምቃ ፡ በደም ።
አንድ ፡ ሰው ፡ አየና ፡ ቀርቦ ፡ ጠየቃት ፤
የቱን ፡ ልንቀልልሽ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ።
ሁሉንም ፡ ለማውጣት ፡ አልተቻለኝም ፤
ቸኩያለሁና ፡ ጊዜ ፡ አላገኝም ።
ከነቀልህልኝስ ፡ አለችው ፡ ጌታዬ ፤
መጀመሪያ ፡ ይውጣ ፡ የመቀመጫዬ ።
ቂጤ ፡ መሬት ፡ ዐርፎ ፡ ትንፋሼን ፡ ካገኘሁ ፤
የቀረውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ አወጣዋለሁ ።
ይህንን ፡ ተናግራ ፡ ዝንጆሮ ፡ ዐረፈች ፤
እሾሁን ፡ በተራ ፡ እያወጣች ፡ ጣለች ።

የመቀመጫችን ፡ የሀገር ፡ ነገር ፤
ከሌላው ፡ ጣጣችን ፡ ይቅደም ፡ ይጀመር ።
በጣም ፡ ቢቸግረን ፡ በጣም ፡ ቢከፋን ፤
ይህንን ፡ ታግሠን ፡ ላገር ፡ ከለፋን ፤
ኋላ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ አንቅሪጥ ፡ ተስፋን ።

ዮ. አ. ወ.

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ የዝንጀሮ ፡ ዘዴ ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ የመቀመጫዬን ፡ ማለቷ ፡ የምን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ?

በደግ ፡ አድራጊ ፡ ክፉ ፡ መዋል ፡ አይገባም ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ክፉ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሌባ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አትለፈኝ ፤ ሆዴን ፡ ቍርጠት ፡ አሞኝ ፡ ለመሄድ ፡ ያቃተኝ ፡ ነኝ ፤ ቤቴም ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ከተራራው ፡ አጠገብ ፡ ነው ፡ ለመሄድ ፡ ባለመቻሌ ፡ እዚሁ ፡ የምሽት ፡ አውሬ ፡ ሊበላኝ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሲጮህ ፡ በፈረስ ፡ የተቀመጠ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰምቶት ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ቀርቦ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆነህል ፡ ወንድሜ ፡ ያመመህስ ፡ ምንህን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። አታላዩም ፡ ሆድ ፡ ቍርጠት ፡ አሞኝ ፡ እግሬ ፡ አልላወስ ፡ ብሎኝ ፡ እዚህ ፡ እንደ ፡ ተኛሁ ፡ ሊመሽብኝ ፡ ነው ፤ እባክህ ፡ ትንሽ ፡ እን እንኳን ፡ እርምጃ ፡ ስንዝር ፡ ያህል ፡ መንገድ ፡ ወስደህ ፡ ከዚያ ፡ ማዶ ፡ መንደር ፡ አስጠጋኝ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። ያም ፡ ባለፈረስ ፡ በነገሩ ፡ ራርቶና ፡ እዝኖ ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ና ፡ ከፈረሴ ፡ ላይ ፡ ውጣ ፡ አለው ።

አታላዩም ፡ ተነሥቼ ፡ ከፈረሱ ፡ ለመውጣት ፡ ጎይል ፡ የለኝ ምና ፡ ደግፈህ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለህ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ። እሱም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ኖሮ ፡ ከተኛበት ፡ አንቅቶ ፡ በእጁ ፡ ደግፎ ፡ አንሥቶ ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ። ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ልጓም ፡ ይዞ ፡

እየመራ ፡ ሲወስደው ፡ ሳለ ፡ አታላዩ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ በእግርህ ፡ ከመሄድህ ፡ ይልቅ ፡ ልጓም ፡ ይዘህ ፡ እኔን ፡ ስትመራኝ ፡ እንቅፋት ፡ ይመታሀል ። ተሰናክለህም ፡ ብትወድቅ ፡ ጉዳት ፡ ይሆናልና ፡ እርካቡን ፡ አስቆንጥጠኸኝ ፡ ልጓሙን ፡ አሲዘኸኝ ፤ ቀስ ፡ እያልህ ፡ አዘግማለሁ ፡ አለው ።

የፈረሱም ፡ ባለቤት ፡ ደግ ፡ የዋህ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ከለቀቀለት ፡ በኋላ ፡ አታላዩ ፡ ሌባ ፡ ፈረሱን ፡ ኰርኩሮ ፡ ልጓሙን ፡ አላልቶ ፡ አስነሥቶ ፡ በግልቢያ ፡ ሽምጥ ፡ እንግዲህ ፡ ደኅና ፡ ዋል ፡ ሰውዬ ፡ ብሎ ፡ ጋለበ ።

ሲጋልብ ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ተጣርቶ ፡ አንተ ፡ ሰው ፤ ፈረሱንስ ፡ ውሰደው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ ስማኝ ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይሰማው ፡ አለው ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ቢለው ፡ ይኸንን ፡ የሰማ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ለታመመና ፡ ለወደቀ ፡ የደግ ፡ አሳብ ፡ ርዳታ ፤ የርኅራሄም ፡ ሥራ ፡ እንዳያደርግለት ፡ ይፈራልና ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ ጊዜ ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ ልቡ ፡ ተነክቶ ፡ ተጸጽቶ ፡ መልሶ ፡ ፈረሱን ፡ ሰጠው ።

ምክር ፤ ክፉን ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ አለማሰብ ፤ ቢያስቡም ፡ ሳያደርጉ ፡ ተጸጽቶ ፡ መተው ፡ መልካም ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡ የወደቀን ፡ አንሣ ፡ የሞተን ፡ አትርሳ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ኛ ፤ ደግ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ተንኰለኛው ፡ ሌባ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ምን ፡ ይል ፡ ኖሯል ?
፫ኛ ፤ ደጉ ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ ምን ፡ አደረገለት ?
፬ኛ ፤ ተንኰለኛው ፡ ሌባ ፡ ከፈረሱ ፡ ከወጣ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፭ኛ ፤ ሲጋልብ ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ባለፈረስ ፡ ተጣርቶ ፡ ምን ፡ አለው ?
፮ኛ ፤ ተጸጽቶስ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፯ኛ ፤ የመጸጸትስ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ?